ለሰዎች ምሕረት ታሳያለህ?

መመሪያ፦ ይህን መልመጃ ጸጥታ በሰፈነበት ቦታ ሆነህ ሥራ። ጥቅሶቹን ስታነብ በቦታው እንዳለህ አድርገህ አስብ። ሁኔታውን በዓይነ ሕሊናህ ለመሳል እንዲሁም በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱት ሰዎች ሲነጋገሩ ድምፃቸውን ለመስማትና ስሜታቸውን ለመረዳት ሞክር። ታሪኩ ሕያው እንዲሆንልህ አድርግ።
ዋነኞቹ ባለታሪኮች፦ አይሁዳዊ ሰው፣ ካህን፣ ሌዋዊ እና ሳምራዊ ሰው
ታሪኩ በአጭሩ፦ አንድ ሳምራዊ ሰው ጉዳት የደረሰበትን አይሁዳዊ እንደረዳው ኢየሱስ የተናገረው ታሪክ።

1 ሁኔታውን ለማስተዋል ሞክር።—ሉቃስ 10:29-37ን አንብብ።

ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ የሚወስደው መንገድ ምን እንደሚመስል ለመግለጽ ሞክር።

ከታች የተጠቀሱት ሰዎች ፊት ላይ ምን “ይታይሃል”?

የካህኑና የሌዋዊው ፊት

የደጉ ሳምራዊ ፊት

‘ጻድቅ መሆኑን ማሳየት የፈለገው’ ሰው ሲናገር ድምፁ ምን ዓይነት ቃና የነበረው ይመስልሃል? (ቁጥር 25ን እና 29ን አንብብ።)

2 ጥልቅ ምርምር አድርግ።

ኢየሱስን ያዳምጡ የነበሩ ሰዎች ሳምራዊው አንድን አይሁዳዊ በመርዳቱ የተደነቁት ለምን ሊሆን ይችላል? (ዮሐንስ 4:9ን አንብብ።)

ካህኑና ሌዋዊው ጉዳት የደረሰበትን አይሁዳዊ ላለመርዳት ምን ዓይነት ሰበብ አቅርበው ሊሆን ይችላል?

ኢየሱስ፣ ሰውየው በሉቃስ 10:29 ላይ ላነሳው ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ ከመስጠት ይልቅ ይህን ታሪክ መናገር የፈለገው ለምን ይመስልሃል?

www.jw.org/am © 2013 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

3 ከዚህ ታሪክ ያገኘኸውን ትምህርት ተግባራዊ አድርግ።

ከዚህ በታች ስለሰፈሩት ሐሳቦች ምን ትምህርት አንዳገኘህ ጻፍ፦

ምሕረት ማሳየት ማለት ምን ማለት እንደሆነ

ለባልንጀራ ፍቅር ስለ ማሳየት


4 ራስህን ጠይቅ።

ከአኔ የተለየ ዘር ወይም ዜግነት ላላቸው ሰዎች ምን አመለካከት ሊኖረኝ ይገባል?

አንድ ሰው የእኔ አርዳታ እንደሚያስፈልገው ከተገነዘብኩ ምሕረት ምን አንዳደርግ ሊያነሳሳኝ ይገባል?

ከዚህ ታሪክ የማገኘው ለአኔ በጣም አስፈላጊ የሆነው ትምህርት የትኛው ነው? ለምን?

ተጨማሪ ሐሳብ፦ የተከናወነውን ድርጊት በቅደም ተከተል የሚያሳዩ ሥዕሎች ጫር ጫር አድርግ። ከዚያም ስለ አያንዳንዱ ሥዕል መግለጫ ስጥ።



JW.ORG™
ይህን ፒዲኤፍ ከwww.jw.org/am ላይ አውርደህ ማተም ትችላለህ

www.jw.org/am © 2013 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania